# <u>የአማርኛ ግስ ሥነ ምዕላድ በአጭሩ</u>

ድምጾች በአንድ ላይ ተቀናጅተው እንዴት ትርጉም እንደሚሰጡ የሚጠናበት ክፍል ሥነ ቃላት (ሥነ ምዕላድ) ይባላል። ሥነ ቃላት የሚያካትታቸው ርእሶች የቃላት ክፍሎች፣ እርባታ፣ ምሥረታና ጥመራ ናቸው። ***<u>የቃላት ክፍሎች</u>*** የሚባሉት ስም፥ ግስ፥ ቅጽል፥ ወዘተ. ናቸው።

***<u>እርባታ</u>*** ማለት አንድ ቃል ለቁጥር፥ ጾታ፥ ጊዜ፥ ወዘተ. ቅርጹን የሚለዋውጥበት ሂደት ነው።

<u>ምሳሌ</u>:- ቤት ቤቶች ፥ ሄደ ይሄዳል እየሄደ ነው

***<u>ምሥረታ</u>*** ደግሞ ከአንድ የቃል ክፍል ሌላ ቃል የሚፈጠርበት መንገድ ነው።

<u>ምሳሌ</u>:- ረዘመ (ግስ) ረጅም (ቅጽል) ርዝመት (ስም)

***<u>ጥመራ</u>*** ሁለት የተለያዩ ቃላትን በማጣመር አዲስ ቃል የመፍጠር ዘዴ ነው።

<u>ምሳሌ</u>:- ጠጅ ቤት ፥ ዓለም-አቀፍ ፥ ቀዶ ጥገና ፥ ወፍ-ዘራሽ ፥ ሕገ መንግሥት ፥ ሆደ ሰፊ

በዚህ ትምህርት ላይ የምናተኩረው በግሶች ላይ ነው። ምክንያቱም ግሶች በአማርኛና ሴማዊ ቋንቋዎች ውስጥ ያላቸው ቦታ የሰፋና ወሳኝ ስለሆነ ነው።

(1) ግሶች <u>በአገባባቸው</u> በዓረፍተ ነገር መጨረሻ ይመጣሉ፣ <u>ቅርጽን</u> የተመለከትን እንደሆነ ባለቤት አመልካችና ተሳቢ ቅጥያዎችን (በተለይም ሳቢ ግሶች) ያስከትላሉ።

<u>ምሳሌ</u>:- ከበደ ብርጭቆውን <u>ሰበረ</u>። /ስኧብብኧር-ኧ/ [säbbär-ä]

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ብ | ብኡ | ብኢ | ብኣ | ብኤ | ብ(እ) | ብኦ |
| **bä** | **bu** | **bi** | **ba** | **be** | **b(ə)** | **bo** |

(2) በአማርኛና በሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎች <u>ሥርወ ቃል</u> ታላቅ ሚና ይጫወታል። ምክንያቱም የቃላት እርባታ፣ ምሥረታና ጥመራ የተመረኮዘው በሥርወ ቃል ላይ ስለሆነ ነው።

(ሀ) <u>ሥርወ ቃል</u> :- መሠረታዊውን ትርጉም የያዘው አሐድ ነው። ምሳ. /ፍ-ል-ግ/ /ስ-ብ-ር/

በእርባታ፥ ምሥረታ ሆነ ጥመራ ሥርወ-ቃሉ አይለዋወጥም። ሁልጊዜ ቋሚ ነው።

<u>ምሳሌ</u>:- ዘፈነ ዘፈን ዘፋኝ ዘፍኖ መዝፈን አዘፋፈን

(ለ) <u>እግር</u> :- የሥርወ ቃሉ አንዱ ተናባቢ ነው። በ/ፍ-ል-ግ-/ ውስጥ 3 እግሮች አሉ። እግሮቹ በቦታቸው መሠረት መነሻ፣ ቅድመ መድረሻና መድረሻ ናቸው። የአማርኛ ግሶች እግር ከ1 እስከ 7 ይደርሳል። <u>ምሳሌ</u>:- ሻ፥ በላ፥ ዘፈነ፥ መሰከረ፥ አንቃጨለ፥ ተሽከረከረ፥ አንከረባበተ ከ4 በላይ እግር ያላቸው ግሶች በጣም የተወሰኑ ሲሆን የታሪክ ሥነ ልሳን ተመራማሪዎች አብዛኛዎቹ የአማርኛ ግሶች ባለ3 እግር ስለመሆናቸው ማስረጃ አላቸው።

(ሐ) <u>ዓምድ</u> :- የሥርወ ቃልና የዓምድ አናባቢው /ኧ/ ቅንብር ሲሆን ቅጥያዎችን ሊያስከትል የሚችል ነው። ምሳ. /ፍኧልልኧግ-/ → /ፈለግ-/ በዚህ ዓምድ ላይ ባለቤት አመልካች ቅጥያዎችን በመጨመር የዋህ ኀላፊን መምሥረት ይቻላል። <u>ምሳሌ</u>:- /ፈለግ-ሽ/ ፣ /ፈለግ-ን/ ወዘተ. ይህ አናባቢ ማለትም /ኧ/ በተለያዩ እርባታዎች ጊዜ ሊጠፋ ወይም ሊለዋወጥ ይችላል። እንደዚሁም ከጉሮሮና ከላንቃ ድምጾች አጠገብ በመገኘት እነዚህ ድምጾች እንዲለወጡ አድርጓል። ይህንን ከአማርኛ ግሶች ቅርጽ ማየት ይቻላል።

(3) በዋህ ኀላፊ ጊዜ ግሶች ከጥብቀት አኳያ በ2 ይከፈላሉ ፡ አንዱን እግራቸውን <u>የሚያጠብቁና</u> <u>የማያጠብቁ</u>። ላዕላይ መዋቅራቸው ሲታይ ግሶች የሚያጠብቁት <u>ቅድመ-መድረሻ</u> ወይም <u>መድረሻ</u> እግራቸውን ነው። የሚከተሉት ምሳሌዎች ይህንኑ ያስረዳሉ።

(i) <u>የሚያጠብቁ ግሶች</u> <u>የጠበቀው እግር</u>

ምሳ. (1) ዘፈነ /ዝኧፍፍኧን-ኧ/ /zäffänä/ መረቀ /ምኧርርኧቅ-ኧ/ /märräqä/ ቅድመ-መድረሻ

(2) በላ /ብኧልልኣ/ /bälla/ ሰለቸ /ስኧልኧቸቸ-ኧ/ /säläččä/ መድረሻ

በቁጥር (2) ያሉት ግሶች መድረሻቸውን ያጠበቁ መስለው ይታያሉ። ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም። የግሶቹ ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው ሲሆን የድምጽ ለውጥ ተከስቶበታል።

a. በለዐ /ብኧልልኧዕ-/ /bällä‘-/ → /bälla/ (ä‘ → a) በላ bälla-ä bälla (ä → ∅ /a- )

b. ሰለተይ /ስኧልኧትትኧይ-/ /sälättäy-/ → /säläččä/ ሰለቸ säläččä -ä säläččä (ä → ∅ / ä - )

ግሶቹ መድረሻቸውን የጐረዱ ለመሆናቸው ሌላ ማስረጃ በቦዝና በአርእስት ቅርጻቸው ጊዜ /ት/ በተጎረደው ድምጽ ቦታ ትመጣለች። <u>ምሳሌ</u>:- ዘፍኖ ፥ መዝፈን (ነገር ግን በልቶ ፥ መብላት እንደዚሁም ሰልችቶ ፥ መሰልቸት) ከላይ የተሰጠው ማስረጃ የሚያመለክተው ግሶች በሙሉ ቅድመ መድረሻ እግራቸውን እንደሚያጠብቁ ያሳያል ማለት ነው።

<u>(ii) የማያጠብቁ ግሶች</u> :- ጠብቆ የሚነገር እግር የላቸውም። ምሳ. ሄደ፥ ቆመ ፥ ጻፈ

ሄደ /ህኧይይኧድ-ኧ/ häyyäd-ä ቆመ /ቅኧውውኧምኧ/ qäwwäm-ä ጻፈ /ጽኧህህኧፍኧ/ s’ähhäf-ä

እነዚህ ግሶች የማያጠብቁበት ምክንያት ቅድመ-መድረሻው ድምጽና ቀድሞት የመጣው /ኧ/ በአንድነት ሆነው ወደ አናባቢ ስለተለወጡና ሁለተኛው /ኧ/ ስለጠፋ ነው። እነዚህ ግሶች ቅድመ መድረሻ እንደነበራቸው ማስረጃው <u>አስኪያጅ</u> ፥ <u>ቋሚ</u>፥ <u>ጸሐፊ</u> እና የመሳሰሉት ቃላት ናቸው።

(4) ግሶች በእርባታ ጊዜ በሚያሳዩት የጥብቀት ሁኔታ <u>ምድብ “ሀ” (type A)</u> ፥ <u>ምድብ “ለ” (type B)</u> ፥ እና <u>ምድብ “ሐ” (type C)</u> ተብለው ለሦስት ይከፈላሉ። ምድብ “ሀ” በዋህ ኀላፊ ጊዜ ብቻ ቅድመ-መድረሻቸውን ሲያጠብቁ በምድብ “ለ” ያሉት በሁሉም እርባታዎች ያጠብቃሉ፥ ምድብ “ሐ” ደግሞ በየዋህ ኀላፊና በዘንድ አንቀጽ ብቻ ያጠብቃሉ። ከታች ያሉት ምሳሌዎችም ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸው።

| <u>ግስ</u> | <u>ኀላፊ ጊዜ</u> | <u>ቦዝ</u> | | <u>ዘንድ አንቀጽ</u> | |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረስ | därräs-ä | därs-o | ደርሶ | yədärs- | ይደርስ |
| ረበሸ | räbbäš-ä | räbbəš-o | ረብሾ | yəräbbəš- | ይረብሽ |
| ጋለበ | galläb-ä | galləb-o | ጋልቦ | yəgalləb- | ይጋልብ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| <u>ምድብ “ሀ”</u> | ደከመ | ቀረበ | አገባ | ሠራ | ቀረ | ፈጀ |
| <u>ምድብ “ለ”</u> | ፈለገ | ወፈረ | አሰበ | ለካ | ለየ | ሸኘ |
| <u>ምድብ “ሐ”</u> | ጋለበ | ባከነ | ዘረጋ | ዋኘ | ሳሳ | መሰከረ |

(5) ግሶች ለ<u>ጊዜ</u>፥ ለ<u>መደብ</u>፥ ለ<u>ጾታ</u>፥ ለ<u>ቁጥር</u>ና ለ<u>አንቀጽ</u> ቅጥያዎችን በመጨመር ቅርጻቸውን ይለዋውጣሉ።

<u>ጊዜ</u>:- ድርጊቱ የተፈጸመበትን፥ የሚፈጸምበትን ወይም በመፈጸም ሂደት ላይ እንዳለ ያመለክታል። በዚህ ዓይነት <u>የዋህ ኀላፊ</u>፥ <u>የቅርብ ኀላፊ</u>፥ <u>የሩቅ ኀላፊ</u>፥ <u>የማያቋርጥ የአሁን ጊዜ</u>፥ <u>የማያቋርጥ ኀላፊ</u> ጊዜና <u>የአሁን/የትንቢት</u> ጊዜ ናቸው።

| <u>የዋህ ኀላፊ ቅጥያዎች</u> | | **-ku** | **-k** | **-š** | **-ä** | **-n** | **-aččəhu** | **-u** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| <u>የዋህ ኀላፊ</u>:- ዘፈን- | zäffän- | ዘፈን-ኩ | ዘፈን-ክ | ዘፈን-ሽ | *ዘፈን-ኧ* | ዘፈን-ን | *ዘፈን-አችሁ* | *ዘፈን-ኡ* |
| በላ- | bälla- | በላ-ሁ | በላ-ህ | በላ-ሽ | በላ (በላ-ኧ) | በላን | በላ-ችሁ | በሉ (በላ-ኡ) |

የድምጽ ለውጦች :- (1) ክ → ህ /አናባቢ- (2) አናባቢ-አናባቢ → አናባቢ ∅ (ደካማ አናባቢ

<u>አዘጋጅ</u> :- *ዶ/ር አንበሴ ተፈራ*